# Übersetzung der Dialoge

# የውይይት ክፍል ትርጉም

**ምዕራፍ 1**

***ሙዚቃው ግሩም ነው!***

*በመጀመሪያ ከአንድ ዜማ የተወሰደች አጭር ክፍልን ታደምጣላችሁ። የተጫወተችው ከ 1901-1992 የኖረችው ዝነኛ የጀርመን ተዋናይና ዘፋኝ ነበረች። ግጥሙ በሀጋዊ ገደብ ምክንያት ከጀርመንኛ ውጭ በሌላ ቋንቋ ሳይተረጎም ቆይቷል።*

*ድርጊት 1: ጥቂት ሰዎች መንገድ ላይ ሆነው አንድ የአደባባይ ሙዚቀኛ የሚጫወተውን ይሰማሉ። ስለ ሙዚቃው የሚናገሩት እንደሚከተለው ነው።*

| | |
|---|---|
| 1. Frau: | ኡሁ፣ በጣም ደስ ይላል! |
| 2. Frau: | አስደናቂ! |
| 1. Junge: | ሙዚቃው ድንቅ ነው! |

| | |
|---|---|
| *ድርጊት 2:* | *ከሰዎቹ አንዱ ሲጋራ ይጠይቃል።* |
| 2. Junge: | ለኔ የሚሆን ሲጋራ አለህ? |
| 1. Junge: | ምን ትፈልጋለህ? |
| 2. Junge: | ለኔ የሚሆን ሲጋራ አለህ? |
| 1. Junge: | አዎን፣ ይሄውልህ |

| | |
|---|---|
| *ድርጊት 3:* | *ወጣቱ ሰው እሳትም ይጠይቃል።* |
| 2. Junge: | እሳትስ አለህ? |
| 1. Junge: | እሳት? አይ፣ የለኝም |
| Mann: | ቆይ አንዴ፣ እኔ እሳት አለኝ |
| 2. Junge: | አመሰግናለሁ |

**ምዕራፍ 2**

**ስሜ ኤክስ ነው**

*በዚህ በሁለተኛው ምዕራፍ የቋንቋ ኮርሳችን ዋና ዋና ተዋንያን ራሳቸውን ያስተዋውቃሉ። የሆቴል ሃላፊዋ ወሮ-በርገር ትጀምራለች።*

| | |
|---|---|
| Frau Berger: | መልካም፣ ስሜ በርገር ይባላል። ሊዛ በርገር! እዚህ የሆቴል አውሮፓ አስተዳዳሪ ነኝ |
| Ex: | እርሷ መዝፈን ትወዳለች! |
| Frau Berger: | አዎን፣ ዕውነት ነው |

*ከዚያም የፈጠራ ምስል የሆነችው ኤክስ ራሷን በግጥም መልክ ታስተዋውቃለች።*

| | |
|---|---|
| Ex: | ማን እንደምባል ሁሉም ያውቃል<br>ስሜ ኤክስ ነው፣ ሴት ወይዘሮ ነኝ<br>ልታዩኝ አትችሉም፣ እሱን የሚረዳ ማንም የለም<br>ግን ልትሰሙኝ ትችላላችሁ፣ እሱን ማንም ይመሰክራል! |
| Andreas: | በጥባጭም ናት |

*የሚቀጥለው አንድሬያስ ሼፈር ነው። ሆቴል አውሮፓ ውስጥ በእንግዳ ተቀባይነት የሚሰራ ሲሆን ከዚሁ በተጨማሪም የጋዜጠኝነት ሙያን ይማራል።*

| | |
|---|---|
| Andreas: | መልካም፣ ሰሜ አንድሬያስ ነው። አንድሬያስ ሼፈር! ሆቴል አውሮፓ<br>ውስጥም እሰራለሁ።<br>እንግዳ ተቀባይ ነኝ |
| Ex: | ግን እኮ ተማሪም  ነህ |
| Andreas: | እርግጥ ነው ኤክስ፣ እሱን አውቀዋለሁ! |
| Ex: | ግን ሁሉም አድማጮች አያውቁም |
| Andreas: | ግን አሁን ያውቃሉ! አንድሬያስ ሼፈር ነኝ። ሆቴል አውሮፓ ውስጥ<br>በእንግዳ ተቀባይነት<br>አሰራለሁ፣ ጋዜጠኝነትም እማራለሁ። በቂ ነው? |
| Ex: | *(ትተነፋፍሳለች)* |

*ሃና ክላዘን ደግሞ በሆቴል አውሮፓ ክፍል አጽጂ ናት።*

| | |
|---|---|
| Hanna: | ተራው የኔ ነው? |
| Ex: | አዎን |
| Hanna: | ደህና፣ ስሜ ሃና ነው። ሃና ክላዘን! የሆቴል አውሮፓ ክፍል አጽጂ ነኝ።<br>እዚህ መስራቴን<br>አወደዋለሁ። በዙ ሰዎች ይመጣሉ |
| Ex: | (ጥቂት በማሬዝ) እና ሁልጊዜም ደጎች ናቸው |

*በርሊን ነዋሪ የሆነው ዶር-ትሁርማን የሆቴል አውሮፓ ቋሚ እንግዳ ነው።*

| | |
|---|---|
| Dr. Thürmann: | አዎን-ሁሌ አይደለም! ግን ደግና በጥቂቱም ቢሆን አንጋፋ ሰው ነኝ።<br>እንግዲህ የሆቴል አውሮፓ እንግዳ ስሆን እዚህ አኸን አዘውትሬ እመጣለሁ |
| Ex : | *(ያለ ትዕግስት)* ስምህ? |
| Dr. Thürmann: | ምን አባክሽ? |
| Ex: | ስምህ ማነው? |
| Dr. Thürmann: | አሃ፣ አዎ ትሁርማን እባላለሁ |
| Ex: | ዶር-ትሁርማን ነው። ጆሮው ደህና አድርጎ አይሰማም |

## ምዕራፍ 3

### ይዘኸኝ ትሄዳለህ?

አንድሬያስ ሰንበቱን ከስራ ነጻ ነው። ወደ ብራስልስ የሚጓዝ ሲሆን ክፍል አጽጂዋን ሃናን አበሮ ይወስዳታል።

| | |
|---|---|
| Andreas: | ደህና እንግዲህ፣ መልካም የሣምንት መጨረሻ ወሮ-በርገር! |

| | |
|---|---|
| Frau Berger: | አመሰግናለሁ ለአንተም እንዲሁ! መልካም ጊዜ በብራስልስ! |
| Andreas: | አመሰግናለሁ |
| Hanna: | ምን? ብራስልስ ትሄዳለህ?! |
| Andreas: | አዎን፤ እዚያ ቀጠሮ አለኝ |
| Hanna: | ንገረኝ፤ በመኪና ነው የምትሄደው? |
| Andreas: | አዎን |
| Hanna: | ብራስልስ ውስጥ የምትገኝ ባልንጀራዬን መጠየቅ እፈልግ ነበር፤ ይዘኸኝ ትሄዳለህ? |
| Andreas: | እንዴታ! ነገ ጧት በስምንት እንነሳለን። ቤትሽ መጥቼ እወስድሻለሁ |
| Hanna: | ግሩም ነው! በጣም አመሰግናለሁ አንድሬያስ። ሰላም፤ እንግዲህ እስከነገ! |
| Andreas: | እስከነገ! |

*ሁለቱ ወደ ብራስልስ በማምራት ላይ እንዳሉ አንድሬያስን ትራፊክ ተቆጣጣሪ ፖሊስ ያስቆመዋል። አንድሬያስ መኪናውን ከመጠን ባለፈ ፍጥነት እያሽከረከረ ነበር።*

| | |
|---|---|
| Andreas: | አይ ጉድ፤ ይህ ነበር የቀረኝ |
| Hanna: | ምኑ? |
| Andreas: | ፖሊስ! ለቀጠሮዬ እንደምደርስ ተስፋ አለኝ *(አንድሬያስ መኪናውን ያቆማል)* |
| Polizist: | ጤናይስጥልኝ፤ የትራፊክ ቁጥጥር ነው። መንጃ ፈቃድዎን ይስጡኝ! እስቲ መብራት ያብሩ! ኦኬይ፤ ሁሉም ትክክል ነው። አቶ ሺፈር ምን ያስባሉ፤ በምን ፍጥነት ነው ይነዱ የነበሩት? |
| Andreas: | አላውቅም |
| Polizist: | 130 ኪሎሜትር! |
| Andreas: | ሊሆን ይችላል |
| Polizist: | ግን እዚህ በሰዓት መቶ ብቻ ነው መንዳት የሚፈቀደው። ሰሌዳውን አላዩም? |
| Andreas: | የለም፤ አዝናለሁ |
| Polizist: | ደህና፤ እሱ ሊረዳዎት አይችልም። 80 ማርክ መቀጮ መክፈል ይኖርብዎታል |

**ምዕራፍ 4**

**የከተማ ካርታ አለዎት?**

*ሁለት የትዳር ጓደኞች አኸን ዋና ጣቢያ ይደርሱና በዚያው ወደሚገኘው የቱሪስት መረጃ ቢሮ ይሄዳሉ።*

*ማስታወቂያ በድምጽ ማጉያ:*
*አኸን፤ አኸን ዋና ጣቢያ! ባቡሩ ጉዞውን የሚያበቃው እዚህ ነው። ወደ ኮሎኝ የምትቀጥሉ መንገደኞች ረድፍ ሶስት ላይ የሚቆመውን ባቡር መያዝ ትችላላችሁ። የሚነሳው በ 18.02 ሰዓት ነው።*

| | |
|---|---|
| Herr Frisch: | ጎሽ አበቃ! ነይ በይ፤ አሁን በቅድሚያ የከተማ ካርታ ያስፈልገናል |
| Frau Frisch: | ልትገዛው ትፈልጋለህ? |
| Herr Frisch: | አይ፤ ያቺ „I" የምትለው ፊደል አትታይሽም? የመረጃው ማዕከል እዚያ ነው። እዚያ በእርግጥ የከተማ ካርታ ይኖራል |
| Angestellte: | ልረዳዎት እችላለሁ? |
| Herr Frisch: | አዎን እባክዎ፤ የከተማ ካርታ አለዎት? |
| Angestellte: | *(አንድ የከተማ ካርታ ይከፍትና ይዘቱን ያስረዳል)* አዎን፤ እንዴታ |

| | |
|---|---|
| | ይመልከቱ-ይህ ዋና ባቡር ጣቢያው ነው። አሁን ያሉት እዚህ ነው። ይህ ደግሞ የከተማው ማዕከል ነው። ይንገሩኝማ፤ ለመሆኑ ሆቴል ይዘዋል? |
| Frau Frisch: | አዎን፤ ሆቴል አውሮፓ |
| Angestellte: | እሱ እዚሁ ቅርብ ነው |
| Herr Frisch: | እንዴት አመቺ ነው! |
| Frau Frisch: | ግሩም! ከፍተኛ ምስጋና! |

*ሁለቱ የትዳር ጓደኞች ሆቴል አውሮፓ ይደርሱና በቅርብ የሚገኝ ምግብ ቤት እንዳለ ይጠይቃሉ።*

| | |
|---|---|
| Herr Frisch: | ቀርብ ያለ ደህና ምግብ ቤት ሊጠቁሙን ይችላሉ? |
| Andreas: | በደስታ! እዚያች ጥግ ላይ አንድ ፒሴሪያ አለ |
| Herr Frisch: | ኦህ መልካም። የጣሊያን ምግብ ሁሌም ይጥመኛል |
| Frau Frisch: | አይ፤ በዕውነት ይቅር! ፒሰሪያማ በየቦታው ሞልቷል |
| Andreas: | ምናልባት የፈረንሳይ ምግብ መሞከር ይፈልጋሉ? |
| Frau Frisch: | አይ፤ አመሰግናለሁ። የጀርመን ምግብ ነው የምንፈልገው |
| Andreas: | እንግዲያው *Postwagen* ምግብ ቤትን እመርጥልዎታለሁ። ምግቡ ጥሩና ርካሽ ነው |
| Herr Frisch: | አመሰግናለሁ፤ እንሞክረዋለን! |

**ምዕራፍ 5**

**መጠጦቹን እከፋፍላለሁ**

*አንድሬያስ ልደቱን እያከበረ ነው። ጓደኞቹንም ከቤቱ ጋብዟል።*

| | |
|---|---|
| Freunde: | *(እብረው ይዘፍናሉ)* መልካም ልደት ይሁንልህ... |
| Freundin: | መልካም ልደት! |
| 1.Freund: | ልባዊ ምኞቴ ይድረስህ! |
| Andreas: | አመሰግናለሁ! ግቡ! |
| 1.Freund: | ይኼውልህ ስጦታህ! |
| Freundin: | እዚህም ሌላ አለህ! |
| 2.Freund: | እዚህም ሌላ! |
| Andreas: | አመሰግናለሁ። *(የታሸጉ ስጦታዎቹን መክፈት ይጀምራል)* ይህ ስዕል ግሩም ነው! አመሰግናለሁ ማርቲን! እዚያ ውስጥስ ምንድነው ያለው? |
| Freundin: | ክፈተው እስቲ! |
| Andreas: | *(ፌኡክ ብሎ ያነባል)* ጊንጥ |
| Freundin: | ኮከብ ማውጫ ነው፤ አንድሬያስ። ያንተ ኮከብ! ጊንጥ ነህ እኮ |
| Andreas: | አዎን፤ ልክ ነው። *(ማንበብ ይጀምራል)* በጊንጥ የሚመሰል ሰው ሚስጥርን ማወቅ ይጥራል። ነገሮችን ጠለቅ ብሎ ከበስተጀርባ ለመመልከት ይፈልጋል |
| Freundin: | ረጋ ብለህ አንብበው |
| Andreas: | እና ከዚያ ስለራሴ ሁሉንም አውቃለሁ፤ አይደል? |
| Freundin: | ምናልባት |

*የአንድሬያስ ጓደኞች መብላት፤ መጠጣትና ማውራት ይጀምራሉ።*

| | |
|---|---|
| Andreas: | እንግዲህ ምግቡ ይኼውና |

Freundin: ግሩም! በጣም ርቦኛል
Andreas: እዚህ ደግሞ ብርጭቆ፣ ማንኪያ፣ ሹካ ወዘተ. አሉላችሁ
1.Freund: እኔ ደግሞ መጠጦቹን አከፋፍላለሁ። ማን ጭማቂ ይፈልጋል?
2.Freund: እኔ!
Freundin: ቪኖም አለ?
Andreas: እንዴታ! ቀይ ወይስ ነጭ ነው የምትፈልጊው?
Freundin: ቀይ ቪኖ እመርጣለሁ
1.Freund: የዕጅ-አፍ መጥረጊያ ወረቀት እፈልጋለሁ። የለም እንዴ?
Freundin: ሰሃኖቹ የት ናቸው? የቀረ ሰሃን የለም!
2.Freund: ይሄው እዚህ አሉ! ሙዚቃስ የለም?
Andreas: አለ!

## ምዕራፍ 6

**የተወለደበትን ቀን አያውቀውም?**

*አንድሬያስ ወር-በርገር ልደቱን ምክንያት በማድረግ ለሸለመችው መጽሃፍ ከልብ ያመሰግናል።*

Frau Berger: ጤናይስጥልኝ፣ አቶ ሼፈር
Andreas: ጤናይስጥልኝ፣ ወር-በርገር። ለመጽሃፉ በጣም አመሰግናለሁ!
Hanna: ምን መጽሃፍ?
Frau Berger: ትናንት የአቶ ሸፈር የልደት ቀን ነበር። እና...
Hanna: ልደትህ ነበር? በል ዘግይቶም ቢሆን መልካም ዕድል!
Andreas: አመሰግናለሁ! ደህና፣ መጽሃፉ ውስጥ የሚገኝ አንድ ታሪክ በተለይ ደስ ብሎኛል
Frau Berger: የትኛው?
Andreas: በሲናዚ. ዲክሜን የተደረሰ ታሪክ። (የልደት ቀን የለም፣ ውህደት የለም) የሚል ነው
Hanna: ምን አልክ? ከማን?
Andreas: የአንድ ቱርካዊ ታሪክ ነው። የትውልድ ቀኑን አያውቅም
Hanna: ምን? የተወለደበትን ቀን አያውቅም?

*አንድሬያስ በመጽሃፉ ውስጥ የሚገኝ አንድ ታሪክን አንስቶ ያወሳል። ርዕሱ (የልደት ቀን የለም፣ ውህደት የለም) የሚል ነው። ቱርካዊው የመጽሃፉ ደራሲ. ሲናዚ. ዲክሜን ይባላል።*

Andreas: ታሪኩ እንዲህ ይጀምራል፣ „የትውልድ ቀን የለኝም። እርግጥ ፓስፖርቴ ውስጥ አንድ ቀን ሰፍሮ ይገኛል። ግን ዕውነተኛ የልደት ቀኔ አይደለም። ይፋ የልደት ቀን ብቻ ነው“
Hanna: ከዚያስ?
Andreas: ዲክመን በመጀመሪያ እናቱን ይጠይቃል። እርሷም ታወጣ ታወርድና እንዲህ ትላለች፣ „በዚያን ዕለት የነበረን በሬ ይጠፋል“። ከዚያም ስለ በሬው ማውራት ትቀጥላለች። ... ግን የትውልድ ቀኑና ዓመተ-ምሕረቱ አይመጣላትም

*ደራሲው ሲናዚ. ዲክሜን የትውልድ ቀኑን ለማወቅ ብዙ ጥረት ያደርጋል። ማንኛውም ሰው በዚያ ዕለት የተፈጸመ የሆነ ነገርን ማስታወስ ይችላል። ግን ትክክለኛውን የልደት ቀን ማስታወሱ ነው ችግሩ።*

Andreas: ዲክመን እህቱን ይጠይቃል። አርሷም እንዲህ ትላለች፣ “እርግጥ ነው

አውቃለሁ፣ ባሊን ለመጀመሪያ ጊዜ ያየሁት በዚያን ዕለት ነው”- ከዚያም ታወራለች፣ ታወራለች... ግን ቀኑና ዓመቱ ትዝ አይላትም። ዲክሜን አማቹን፣ አስተማሪውን፣ የመንደሩን አንጋፋ ይጠይቃል። ሁሉም መተረኩን ይተርካሉ። ሆኖም ዲክሜን የልደት ቀኑን ለማወቅ ሳይችል ይቀራል

Hanna: እንግዳ ነገር ነው

Andreas: የለም፣ የተለየ መሆኑ ብቻ ነው ነገሩ!

ምዕራፍ 7

**ማውጫውን ልትሰጪኝ ትችያለሽ?**

*ሁለት የትዳር ጓደኞች አኸን ውስጥ ምን እንደሚገኝ ለማወቅ የቱሪስት መረጃ ደብተሮችን ያገላብጣሉ።*

Herr Frisch: ስለ አኸን መረጃ የሚሰጥ አንድ ደብተር አለሽ - አይደል?

Frau Frisch: አንድ? አራት አለኝ!

Herr Frisch: ደብተሮቹን ስጪኝ እስቲ እባክሽ!

Frau Frisch: አንድ አፍታ ታገሰኝ፣ እነዚሁልህ!

Herr Frisch: *(ደብተሮቹን እያገላበጠ አንዳንድ መረጃዎችን ጮክ ብሎ ያነባል)* አኸንን ይወቁ! አኸን- በአውሮፓ እምብርት ላይ ያለች፣ ኔዘርላንድና ቤልጂግ አጠገብ የምትገኝ ከተማ

Frau Frisch: እሱን ቀድሞ እናውቀዋለን!

Herr Frisch: አኸን- የሥነ-ጥበብ ከተማ

Frau Frisch: የሚማርክ አይደለም!

Herr Frisch: አኸን - የማገገሚያና የፍልውሃ ከተማ

Frau Frisch: እሱ አያስፈልገንም

Herr Frisch: አኸን – የጉባዔ ማዕከል

Frau Frisch: ስራ ከሆነ ቤት ልሰራ እችላለሁ

Herr Frisch: አኸን የምትጎብኚሽ ብዙ ነገር አላት

Frau Frisch: አንተስ ምንድነው የምታቀርብልኝ?

Herr Frisch: አኸን- የደስ ደስ ያላት ከተማ፣ የግብይት ገነት ናት። ይህን አንቺ የምትወጂው ይመስለኛል

Frau Frisch: ደህና፣ በጉጉት እጠብቃለሁ

Herr Frisch: ለጎብኚዎቻችን በደስታ ተጨማሪ መረጃ እንሰጣለን

*ወሮ-ፍሪሽ አንድ ሌላ የመረጃ ደብተርን እያገላበጠች ትመለከታለች።*

Frau Frisch: (ጮክ ብላ ታነባለች) አኸንን እናሳያችሁ! ዘመናዊና ጥንታዊውን ይመልከቱ! የከተማ ጉብኝታችን የሚጀምረው ከካቴድራሉ ነው። *(ወደ ባለቤቷ ዞር በማለት)* ይሄውልህ፣ ይሄ ላንተ ነው!(ማንበብ ትቀጥላለች)የሚያስፈልጋችሁ ጥሩ መንፈስና እርግጥ ጥቂት ገንዘብ ነው። እና መነጽር መያዝ አትርሱ! *(ወደ ባለቤቷ ዞር በማለት)* አንተ እኮ ሁሌ ነው መነጽርህን የምትረሳው። ይሄው- ልስጥህ። አሁኑኑ ኪስህ ውስጥ ክተት! *(ማንበብ ትቀጥላለች)* እንግዲህ ጉዞው ሊጀምር ይችላል

Herr Frisch: አዎን፣ እንሂድ እንግዲህ!

**ምዕራፍ 8**

**ስለርሱዋ ከሰማሁ ብዙ ቆየሁ**

*አንድሬያስ፥ ዶር-ትሁርማንና ወሮ-በርገር ከአንድ ቡና ቤት ተቀምጠዋል። ዶር-ትሁርማንና ወሮ-በርገር የማትታየዋ ኤክስ የት እንደደረሰች ይጠይቃሉ። ኤክስ ድንገት የተሰወረችው ሶስቱ በአንድ የዕለት ጉዞ ላይ እንዳሉ ነበር።*

| | |
|---|---|
| Dr. Thürmann: | የሁለተኛ ድምጽህ ነገር ከምን ደረሰ? |
| Frau Berger: | አዎን፥ ምን ነክቷት ነው ኤክስ? ተመለሰች ወይ? |
| Andreas: | አይ፥ አልተመለሰችም። ስለርሷ ምንም አልሰማሁም |
| Frau Berger: | ያኔ ነበር እኮ የጠፋችው፥ ግን ለምን? |
| Andreas: | ምንም የማውቀው ነገር የለም! |
| Dr. Thürmann: | ይበሉ እስቲ፥ ይሄ ደግሞ ምን ዓይነት ታሪክ ነው? ሁለተኛ ድምጽ-ኤክስ? ጨርሶ ምንም አይገባኝም |
| Andreas: | ደህና፥ ታሪኩን እነግርዎታለሁ። ግን-የማይታመን ነው። ተረት ... |
| Frau Berger: | መልካም፥ በል እስቲ ንገረን! እኔም እኮ ገና አላውቀውም |

*አንድሬያስ አንደ ኤክስ ድንገት ወደርሱ ስለመጣችባት ምሽት እንደገና ያወሳል። ቤቱ ጋደም ብሎ አንዲት መጽሃፍ እያነበበ ነበር። ኮሎኝ መዳረሻ ላይ ይኖሩ እንደነበር ስለሚተረትላቸው በጎ መናፍስት- „ሃይንሰልሜንሽን"*

| | |
|---|---|
| Andreas: | ከቤቱ ሆኜ ሙዚቃ እያደመጥሁ ስለ ሃይንስልሜንሽን አነብ ነበር። እነዚህ በጎ መናፍስት ሌት ሌት እየመጡ የስዉን ስራ ያከናውኑ ነበር ይባላል። አዎን፥ ትንሽ እንደማለም ያደርገኝና ምነው እኔም እንዲህ የሚረዳኝ ባገኘሁ እላለሁ |
| Dr. Thürmann: | ከዚያስ? |
| Andreas: | ኤክስ ትከሰታለች |
| Dr. Thürmann: | ምን ማለትዎ ነው- „መከሰት" ሲሉ? |
| Andreas: | ድምጽ እሰማለሁ፥ ግን ላያት አልቻልኩም። ብቻ በአጭሩ ትመጣለች |
| Frau Berger: | ከመጽሃፍህ ነው የተከሰተችው ማለት ነው? |
| Andreas: | አዎን፥ እና ኤክስ ብዬ እሰይማታለሁ። ኤክስ በላቲን ከአንድ ነገር የመነጨ የማለትን ያህል ነው |
| Frau Berger: | እንግዲህ እርሷ ሁለተኛ ድምጽህ መሆኗ ነው? |
| Dr. Thürmann: | ታሪኩ አስገራሚ-አስደናቂም ነው |

**ምዕራፍ 9**

**አንድ ዜማ ዘፈንኩላት**

*ዶር-ትሁርማን፥ ወሮ-በርገርና አንድሬያስ በራይን ወንዝ ላይ በመርከብ ስላደረጉት ጉዞ መለስ ብለው ያስባሉ። ኤክስም አብራቸው ነበረች።*

| | |
|---|---|
| Dr.Thürmann: | አብረን የመርከብ ጉዞ አድርገን ነበር |
| Andreas: | ኤክስ በጣም ነበር የተደሰተችው |
| Frau Berger: | ከዚያም የሎረላይን ቋጥኝ እናልፋለን |
| Andreas: | እና ኤክስ ድንገት፥ „ሎረላይ? አውቃታለሁ! አጅግ የተዋበች ነበረች!" ትላለች |

Frau Berger: እኔም ስለ ሎረላይ የተደረሰውን ዜማ አዘፍንላታለሁ
Andreas: ከዚያም የመርከቡ መሪ (እርሱ እንዳለው በመናገር) ጥንት ቋጥኙ ውስጥ
ዋሻ ይገኝ ነበር። እና ሃይንሰልሜንሽንም እዚያው ነበር የሚኖሩት
Dr.Thürmann: አፈ-ታሪኩ እንደሚለው!

*ሶስቱም በዚያ ጉዞ የተሰወረችው ኤክስ የት ደርሳ ሊሆን እንደሚችል ያስባሉ።*

Andreas: ወዲያውኑ ኤክስን፣ ይህን ታውቂ ነበር? ስል እጠይቃታለሁ ግን
መልስ አትሰጠኝም። ልክ መጀመሪያ ድንገት እንደመጣች ሁሉ አሁንም
ድንገት ትጠፋለች
Dr.Thürmann: ህም
Frau Berger: ግን እኮ ይህ ግልጽ ነው!
Andreas: ምን?
Frau Berger: ሃይንሰልማንሽንን እየፈለገች ነው!
Andreas: እንዴት ሊሆን ይችላል?
Dr.Thürmann: ምክንያቱ የርሷ ታሪክ መሆኑ ነው፤ ኤክስና ሃይንሰልሜንሽን!
Andreas: ምናልባት! እና አሁን ምን ላድርግ?
Frau Berger: *(ሳቅ በማለት)* መጠበቅና ማሰብ!
Andreas: *(ለራሱ)* በጣም እወዳታለሁ
Dr. Thürmann: ነገ ወደ በርሊን እንደምጊዝ ያውቃሉ። ወጣት ሰው፤
አብረን ወደ በርሊን እንሂድ-ከኤክስ ጋር ወይም ያለ ኤክስ!

**ምዕራፍ 10**

**ክፍል ለማዘዝ እፈልጋለሁ**

*የሆቴል ክፍል መያዝ ወይም ማዘዝ በመሰረቱ ቀላል ነገር ነው ...*

Mann: ጤናይስጥልኝ እንደት አድሩ፣ ሺረር እባላለሁ። ባለ ሁለት አልጋ ክፍል
ማዘዝ ፈልጌ ነበር፣ ከግንቦት አንድ እስከ ሶስት!

*አንዳንዴ ግን አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ ለቤተሰቢ ክፍል ለማዘዝ ከፍራንክፈርት ወደ ሆቴሉ የምትደውለው ሴትዮ የገጠማት ሁኔታ እንደሚያሳየው*

*(ስልኩ ይደወላል)*
Andreas: ሆቴል አውሮፓ፤ ጤናይስጥልኝ
Frau: ጤናይስጥልኝ፣ ቢከር እባላለሁ። የምደውለው ከፍራንክፈርት ነው።
ባልንጀራዬ አንዴ እናንተ ዘንድ አርፋ ነበር። በጣም እንደረካች ነው የነገረችኝ
Andreas : ይህን ስሰማ በጣም ደስ ይለኛል-ምን ላደርግልዎት እችላለሁ?
Frau: ባለቤቴ ደውይ ብሎኝ ነው። ወደ እኽን ለመምጣት አስበን ነበር። እና ቀድሜ
አንድ ክፍል ለማዘዝ እፈልጋለሁ። የምንመጣው ከሁለት ሕጻናት ጋር ነው።
ለመሆኑ እኛው ክፍል ውስጥ አብረው ሊተኙ ይችላሉ?
Andreas: አዎን፤ እንዴታ! እሱ አስቸጋሪ አይደለም
*(የውሻ ጩኸት ይሰማል)*
Frau: ዝም በል ቢሎ! እርግጥ አንተም አብረህ ትሄዳለህ። አዎን- የኛ ቢሎም አብሮ
ይመጣል
Andreas: ቢሎ? ውሻዎ ነው?

Frau: አዎን- አልሰሙትም?
Andreas: ሰምቻለሁ፤ ግን አስቸጋሪ ነው። በመሰረቱ ውሾች ይዞ መምጣት አይፈቀድም

*አንድሬያስ የቢከር ቤተሰብ መቼ ወደ ሆቴሉ እንደሚመጣና ምን ያህል ጊዜ መቆየት እንደሚፈልግ ይጠይቃል።*

Frau: ግን ቢሎ ጨዋ ውሻ ነው
Andreas: ሀም-ደህና፤ እዚህ መቼ ይደርሳሉ?
Frau: ግንቦት ውስጥ፤ በግንቦት መጀመሪያ፤ አርብ ዕለት
Andreas: አርብ-ግንቦት አንድ ቀን ማለትዎ ነው?
Frau: አዎን
Andreas: እና ምን ያህል ነው የሚቆዩት?
Frau: እስከ ዕሑድ! ሰኞ ተመልሰን ስራ መግባት ይኖርብናል
Andreas: መልካም-አንድ ክፍል ለአራት ሰዎች
Frau: ቢሎስ!
Andreas: ግንቦት አንድ በሚውልበት የሣምንት መጨረሻ። ስለ ቢሎ ገና ከአለቃዬ ጋር መነጋገር ይኖርብኛል። የስልክ ቁጥርዎን ቢሰጡኝ? መልሱን ደውዬ እንግርዎታለሁ
Frau : እሺ፤ ፍራንክፈርት 069 ፤ ከዚያም 98 21 41.
Andreas: አመሰግናለሁ። ደህና ሁኑ

## ምዕራፍ 11

### አተር ትበትን ነበር

*ምዕራፍ 11 ውስጥ የሰፈረው ታሪክ ልብ ወለድ ነው። ኢክስ ሃይንሰልሜንሽንን ትጎበኛለች። ኢክስ ወደ አንድሬያስ የመጣችው ስለነዚሁ በጎ መናፍስት ከሚተርት መጽሃፍ እንጣጥ ብላ በመውጣት ነበር። ኢክስ ሃይንሰልሜንሽን ለምን ሰዎችን መርዳት እንዳቆሙ ለማወቅ ትፈልጋለች።*

Ex: ሃሎ ሃይንሰልሜንሽን፤ መጣሁ እኮ እንደገና!
Heinzelmännchen: ያልተጠበቀ ነገር! ከየት ነው የመጣሺው?
Ex: አሁን ከሰዎች ጋር ነው የምኖረው
Heinzelmännchen: ከሰውልጅ ጋር ማለትሽ ነው
Ex: አዎን፤ እንዴት አወቅሽ?
Heinzelmännchen: እሱ ሚስጥሬ ነው
Ex: አሁን ምንድነው የምታደርጊው?
Heinzelmännchen: *(በመቀለድ)* ንገሪኝ እስቲ? አሁን ጋዜጠኛ ነሽ? ቃለ-ምልልስ ለማካሄድ ትፈልጊያለሽ?
Ex: አይ፤ ግን እባክሽ ንገሪኝ፤ ለምንድነው ሰዎችን መርዳት ያቆማችሁት? ያኔ ምን ተፈጸመ?

*ኢክስ ታሪኩን በሙሉ ትረዳለች። አንዷት ጉጉ የሸማ ሰራ ሰው ሚስት ከቤቷ ደረጃ ላይ አተር ትበትንና ማን ሌት ሌት እየመጣ የባሏን የስፌት ስራ እንደሚያከናውን ለማውጣጣት ትሞክራለች።*

Heinzelmännchen: ያኔ፤ ጥንት ... እንዲህ ነው! ለሰዎች እንሰራ ነበር፤ ለልብስ ሰፊውም ጭምር። ልብሶቹን እንሰፋለት ነበር። ሚስቱ ደግሞ ሲበዛ ጉጉ ነበረች
Ex: እንዴኔ!

Heinzelmännchen: አዎን፤ እንዳንቺ! ግን ሲበዛ ክፉም ነበረች። ከቤቷ ደረጃዎች ላይ አተር ትዘራለች። ብዙ፤ ብዙ አተር። እኛም ተደናቅፈን እንወድቃለን። በጣም የሚያም ነገር ነበር

Ex: ግን ለምንድነው አተሩን የዘራችው?

Heinzelmännchen: የምንሰራው ሌት ነበር። እና የልብስ ሰፊው ሚስት እኛን የግድ ማየት ትፈልጋለች። ታዲያ ስንደናቀፍ ሰማችን። ከዚያም መብራት ታበራለች፤ እኛም በፍጥነት እንሰወራለን

Ex: ለሁል ጊዜ?

**ምዕራፍ 12**

**እስማታዊዋን ቃል አንዴ ማለት ነበረበት**

*ኤክስ እነዚህ የፈጠራ ምስሎች አንድ የራሳቸው ሕግ እንዳላቸው ትረዳለች። ይሄውም ለሰዎች የማይታዩ መሆን እንዳለባቸው ነው።*

Heinzelmännchen: ማንም ሊያየን አይችልም። በማንም መታየት የለብንም

Ex: ግን ለምን? ለምንድነው ማንም ሰው እንዲያያችሁ የማይፈቀድለት?

Heinzelmännchen: ለሰዎች የማንታይ ሆነን ለመኖር ነበር የምንፈልገው። ሕጋችን ነው! ኤክስ-አንቺም የማትታዪ ሆነሽ ለመቀጠል ትፈልጊያለሽ፤ አይደል?

Ex : *(በመደናገጥ)* ኦህ-አዎን፤ ያላንዳች ጥርጣሬ!

*ኤክስ እንዴትና ለምን ለአንድሬያስ ልትከሰት እንደበቃች ትረዳለች።*

Ex: እባክሽ ንገሪኝ፤ ከየት ነው የመነጨሁት?

Heinzelmännchen: ነገሩ ቀላል ነው-ኤክስ። እኛ ነበርን ስለ ሃይንስልሜንሽን ከሚተርተው መጽሃፍ ውስጥ የደበቅንሽ

Ex: እናንተ እኔን??

Heinzelmännchen: አዎን፤ እንደ ልብስ ሰፊው ሚስት ጉጉ የሆንሽ አነስታይ የፈጠራ ምስል

Ex: እንደርሷው ክፉም?

Heinzelmännchen: እሱ የራስሽ ውሳኔ ነው። አንድ ሰው እስማታዊዋን ቃል መናገር ነበረበት። እና አንቺም ከመጽሃፉ ወጥተሽ ከሰዎች ጋር መኖር ነበረብሽ - እንደኛው የማትታዪ በመሆን

Ex: እስማታዊዋ ቃል ምንድናት?

Heinzelmännchen: እሷን ራስሽ ፈልገሽ ማግኘት ይኖርብሻል! አንድሬያስ ነበር ቃሏን የተናገረው። ለዚህም ነው ከርሱ ዘንድ ያለሺው

Ex: ኦህ፤ እውነት?!

**ምዕራፍ 13**

**መኪናዎን የት ነው ያቆሙት?**

*ከሆቴል አውሮፓ እንግዶች አንዱ ወደ እንግዳ መቀበያው ስፍራ ይመጣል። መኪናውን ካቆመበት ቦታ ባለማግኘቱ ተበሳጭቷል።*

(Hotelgast = *የሆቴል እንግዳ*)

| | |
|---|---|
| Hotelgast: | መኪናዬ ጠፋች! |
| Andreas: | መኪናዎ ጠፋች? እርግጠኛ ነዎት? |
| Hotelgast: | እንዴታ እርግጠኛ ነኝ! እኔኮ ዕውር አይደለሁም! |
| Andreas: | እስቲ ጥቂት ያስቡ! የት ነበር ያቆሟት? |
| Hotelgast: | ቢስማርክ አደባባይ ላይ-እዚያች ጥግ |
| Andreas: | ኦህ፤ እሱኮ ማቆም የተከለከለበት ስፍራ ነው |
| Hotelgast: | ምን? አይመስለኝም። ምልክት አላየሁም |
| Andreas: | እኔ ላሳይዎት እችላለሁ |
| Hotelgast: | እሺ. እባክህ-ለማየት እፈልጋለሁ<br>*(አብረው ወደ መንገዱ ይሄዳሉ)* |
| Andreas: | ይሄው ይመልከቱ: ከ 1500 - 1800 ሰዓት ማቆም ክልክል ነው! |
| Hotelgast: | ለማመን አልችልም! |

*የሆቴሉ እንግዳ መኪናውን ያቆመው ትራፊክ በሚበዛበት መንገድ ላይ ነበር። አንድሬያስ በበኩሉ መኪናዋ ተነስታ መወሰዷን ነው የሚገምተው። በትክክል ያልቆሙና ትራፊክን የሚያግዱ አውቶሞቢሎች ዘወትር በፖሊስ እንዲነሱ ይደረጋል።*

| | |
|---|---|
| Andreas: | ምን ያህል ጊዜ ነው እዚያ ያቆሙት? |
| Hotelgast: | ለአጭር ጊዜ ብቻ! ደህና፤ ሚስቴን ተቀብዬ መጣሁና አቆምሁ፤ ከዚያም ዕቃዋን ከሆቴል አደረስሁ |
| Andreas: | እና ከዚያም በቀጥታ ወደ መኪናዎ ተመለሱ? |
| Hotelgast: | አይ፤ ወዲያው አልተመለስኩም |
| Andreas: | ክፍልዎ ውስጥ ምን ያህል ቆዩ? |
| Hotelgast: | ፖሊስ ነህ እንዴ ወይስ ምንድነው ነገሩ? |
| Andreas: | አይ፤ እርግጥ አይደለሁም። ግን እንደምገምተው መኪናዎ በፖሊስ ተነስታ ሳትወሰድ አልቀረችም |
| Hotelgast: | እና እንዴት ነው መልሺ ላገኛት የምችለው? |
| Andreas: | ለፖሊስ መደወል ይኖርብዎታል |
| Hotelgast: | ለምን ወዲያውኑ አልነገርከኝም? |
| Andreas : | ምን? |
| Hotelgast: | ማቆም ክልክል ስለመሆኑ! እኔ የሆቴል አገልግሎት የምለው ይሄን ነው...! |

## ምዕራፍ 14

### ፍሬደሪክ ትዝ ይላቸዋል

*ወሮ-በርገር ለአንድሬያስ ኢጣሊያዊው ደራሲ ሌኦ ሊዮኒ „ፍሬደሪክ" በሚል ርዕስ ስለጻፈው ታሪክ ታወሳለች። ታሪኩ ለክረምት ወራት ቀለብ ስለሚሰበስብ አንድ የሜዳ አይጦች ቤተሰብ የሚያወራ ነው። ከአይጦቹ አንዱ - ፍሬደሪክ – ያልተለመደ ነገር ይሰበስባል። ማለት፤ የጸሃይ ጮራ፤ ቀለማትና ቃላት!*

| | |
|---|---|
| Frau Berger: | አንዴ አንድ የሜዳ አይጥ ቤተሰብ ይኖር ነበር። የበጋው ወቅት ሊያበቃ ይቃረብና አይጦቹ ለክረምት የሚሆን ቀለብ መሰብሰብ ይጀምራሉ። ጥራጥሬ፤ ኦቾሎኒና ገለባ ይሰበስባሉ። ከመካከላቸው አንዱ ፍሬደሪክ ብቻ ምንም አያደርግም። የተቀሩት አይጦች „አንተስ ለምንድነው የማትሰራው ?" ሲሉ |

ፍሬደሪክን ይጠይቁታል። ፍሬደሪክ በበኩሉ „እየሰራሁ እኮ ነው - ለክረምት የጸሃይ ጮራ እሰበስባለሁ“ ሲል ይመልሳል። ጥቂት ቆየት ይሉና ደግሞ „ፍሬደሪክ-አሁንስ ምን እያደረግህ ነው“ ሲሉ ይጠይቁታል። ቀለማትን እየሰበሰብኩ ነው ይላል-ፍሬደሪክ! አሁንም እንደገና ጥቂት ቆየት ይሉና „እያለምህ ነው እንዴ?“ ሲሉ ይጠይቁታል። ፍሬደሪክ „የለም“ ለክረምት ቃላት እየሰበሰብኩ ነው ሲል ይመልሳል።

*ክረምቱ ይመጣል። በጣም ረጅም ነበር። አይጦቹም ቀለባቸውን ፈጅተው ይጨርሳሉ። ታዲያ ፈሬደሪክ በዚህ ጊዜ የሰበሰበውን ልዩ ቀለብ አወጥቶ ለተቀሩት አይጦች ይሸልማል።*

Frau Berger: ክረምት ይገባና አየሩ ድንገት ይቀዘቅዛል። የሜዳ አይጦቹም የፍሬደሪክ ነገር ትዝ ይላቸውና "ፍሬደሪክ፣ ያንተስ ቀለብ ይዞታ እንዴት ነው?" ሲሉ ይጠይቁታል።
„ዓይኖቻችሁን ጨፍኑ" - „አሁን የጸሃይ ጮራ እልክላችሁዋለሁ." ይላል ፍሬደሪክ! የሜዳ አይጦቹ አይኖቻቸውን ሲጨፍኑ ሙቀት ይሰማቸዋል። እና "„ቀልማቱስ?“ ሲሉ ይጠይቃሉ። ፍሬደሪክ „እንደገና ዓይኖቻችሁን ጨፍኑ“ ይልና ስለ ቀያይና ሰማያዊ አበቦች፣ ስለ ቢጫ ገለባ ያወሳል። የሜዳ አይጦቹ ዓይኖቻቸውን ይጨፍኑና ቀልማቱን ያያሉ። „እና የቃላቱስ ነገር?“ ሲሉ አይጦቹ በመጨረሻ ይጠይቃሉ። ፈሬደሪክ ቃላቱን ያወጣና አንድ የአይጦች ታሪክ ይነግራቸዋል። ... ግሩም ነበር። የሜዳ አይጦቹም እጅግ ከመደሰታቸው የተነሳ „ፍሬደሪክ፣ አንተኮ ድንቅ ገጣሚ ነህ“ ሲሉ በአድናቆት ይጮሃሉ።

**ምዕራፍ 15**

**የማትታይና በጥባጭ**

*አንድሬያስ ከቤቱ ተቀምጦ እያዘነ ስለ ኤክስ ያስባል። Sowieso የምትለዋን አስማታዊ ቃል ይናገርናም ኤክስ ድንገት ተመልሳ ትመጣለች።*

Andreas: *(ለራሱ)* ኦህ- ኤክስ፣ ይሄው አሁን የሃይንሰልሜንሽንን መጽሃፍ ይዣለሁ። ግን አንቺ ጠፍተሻል! ያሳዝናል! መሰወርሽ እንድከፋ ነው ያደረገኝ። ገን እኮ ለነገሩ እኔጋ ደስተኛ አልነበርሽ ይሆናል
Ex: ሃሎ፣ ሃሎ - አንድሬያስ
Andreas: ምን ነበር እሱ? የሆነ ሰው ስሜን ጠራ?
Ex: አዎን፣ እኔ! ይሄው እንደገና መጣሁ!
Andreas: ኤክስ? ኤክስ? አንቺ ነሽ?
Ex: አዎን፣ እኔ ነኝ። በቃ አታውቀኝም እንዴ?
Andreas: እርግጥ አውቅሻለሁ! ግን አሁንም አትታዪም!
በይ እስቲ፣ ለመሆኑ ደህና ነሽ?
Ex: አዎን! ሁሉም ነገር መልካም፣ ግሩም፣ ድንቅ ...
Andreas: ደህና፣ መልካም! እንደምሰማሽ ከሆነ አሁንም የቀድሞዋ ኤክስ ነሽ-የማትታዪ ...
Ex: በጥባጭ

*አንድሬያስና ኤክስ ስለ ሃይንሰልሜንሽን ያወራሉ። ኤክስ እንዳገኘቻቸው ለአንድሬያስ አትነግረውም። አንድሬያስ በበኩሉ ሃይንሰልሜንሽን የፈጠራ ምስሎች እንጂ በዕውነት በህይወት ያሉ አለመሆናቸውን ይገልጽላታል።*

Andreas: ኢክስ፣ ይህን ያህል ጊዜ የት ነበርሽ?
Ex: ሃይንሰልሜንሽንን እየፈለግሁ ነበር
Andreas: እና አገኘሻቸው?
Ex: አይ፣ እዚያ አልነበሩም
Andreas: እርግጥ አልነበሩም። ኤክስ - ሃይንሰልሜንሽን፣ እሱ እኮ ታሪክ ብቻ ነው
Ex: እኔስ? እኔም የፈጠራ ታሪክ ነኝ?
Andreas: እሱን ገና አላውቅም። አለሽ፣ ግን አላይሽም!
Ex: አትሞክር! የልብስ ሰፊው ሚስትም ሃይንሰልሜንሽንን ለማየት መፈለጓን ታውቃለህ
Andreas: አውቃለሁ። አተር ረጭታ ነበር
Ex: እና ሃይንሰልሜንሽኖች በሙሉ ይጠፋሉ
Andreas: ግን ኢክስ፣ እኔኮ አተር አልረጭም። ከእንግዲህ መጥፋት የለብሽም!

## ምዕራፍ 16

### ግን ዛሬ የተለየ ነው

*ኤክስና አንድሬያስ በባቡር ከኮሎኝ ወደ በርሊን ይጓዛሉ። ባቡሩ ላይ እንደተሳፈሩም ግንቢያው በ 1248 የተጀመረውን የኮሎኝ ካቴድራል (ዶም) ይመለከታሉ። የካቴድራሉ ግንቢያ በ 1560 በመቀጠል የተጠናቀቀው በ 1842 እና 1880 ዓ.ም. መካከል ነበር። ቤተ-ክርስቲያኑ የሚገኘው ከዋናው ባቡር ጣቢያ አጠገብ ነው። ከዚያው የሚነሱ ባቡሮች በራይን ወንዝ ላይ የሚገኝ ድልድይን እያቋረጡ ይጓዛሉ።*

Andreas: ኢክስ፣ እድለኞች ነን! መቀመጫው ክፍል ባዶ ነው
Ex: መስኮት አጠገብ ለመቀመጥ እፈልጋለሁ
Andreas: እንዴታ!
Ex: ግሩም! እየተንቀሳቀስን ነው! ያ ምንድነው?
Andreas: እሱ ዶም ነው
Ex: የተዋበ ነው!
Andreas: በጣም የቆየም ነው
Ex: ተመልከት! በውሃ ላይ እያለፍን ነው
Andreas: ራይን ወንዝ ነው። ከዚህ ቀድም አይተሽዋል

*ከኮሎኝ የተነሱት አንድሬያስና ኢክስ ጥቅጥቅ ብሎ በተከተመው የሩሀር አካባቢ ያልፋሉ። አካባቢው እስከ 1970 ዓ.ም. ድረስ ዋነኛው የጀርመን ኢንዱስትሪ ማዕከል ነበር። ኢሰንና ቦሁም የከሰል ማዕድን ማውጫ ከተሞች ነበሩ፣ ክሩፕ የተሰኘው የብረታ-ብረት ኢንዱስትሪም በዚያው ነበር ሰፍሮ የሚገኘው። የሩሀር አካባቢ ዛሬ ለጤና ጎጂ የሆነ የኢንዱስትሪ ማዕከል የነበረበት ጊዜ አልፏል። አካባቢው የብዙ ዩኒቨርሲቲዎች፣ የባሕል(ፊልም-ቲያትር-ቤተ-መዘክሩን) እና እጅግ ጠቃሚ የሆነ የተፈጥሮ ጥበቃ ቴክኖሎጂ ምርምር ዘርፍ ማዕከል እየሆነ ነው የመጣው።*

Zugführer: ኢሰን ዋና ጣቢያ!
ቦሁም ዋና ጣቢያ!
ዶርትሙንድ ዋና ጣቢያ!
Ex: ብዙ ከተሞች ናቸውሳ!
Andreas: አዎን፣ እዚህ ብዙ ኢንዱስትሪዎች አሉ። በአካባቢው የሚኖረው ሕዝብም ብዙ ነው
Ex: ኢንዱስትሪ?

Andreas: አዎን! ቀድሞ እዚህ በርከት ያሉ የብረታ-ብረት ኢንዱስትሪዎችና በተለይም የከሰል ማዕድናት ነበሩ። ዛሬ ግን ሁኔታው የተለየ ነው። እርግጥ አሁንም ብዙ ኢንዱስትሪዎች አሉ። ሆኖም ጥቂት ከሰል ነው የሚወጣው። ቦሁም ውስጥ አውቶሞቢሎች ይመረታሉ፤ የዶርትሙንድ ቢራም እንዳለ ነው። የአካባቢው ሰማይ ደግሞ ግራጫ መምሰሉ ቀርቶ እንደገና ሰማያዊ ሆኗል!

*ፌደራሏ ክፍለ-ሐገር ኖርድራይን ቬስትፋሊያ የኢንዱስትሪ ማዕከል ብቻ አይደለችም። ሙንስተርላንድ ለምሳሌ ሰፊ የዕርሻ ልማት አካባቢ ነው። በርከት ያሉ አሳሞችና ፈረሶች ይረቡበታል።*

Ex: ተመልከት! ሜዶቹ ላይ ብዙ አሳሞችና ፈረሶች አሉ!
Andreas: ግልጽ ነው፤ አሁን እኮ ቬስትፋሊያ አውራጃ ገብተናል። እዚህ እምብዛም ኢንዱስትሪዎች የሉም። የሚበልጠው እርሻ ነው

*ኢክስ በርሊን ለመድረስ ገና ምን ያህል ጊዜ እንደቀረ ለማወቅ ትፈልጋለች።*

Zugführer: ቢለፌልድ ዋና ጣቢያ
ሃኖቨር ዋና ጣቢያ
Ex: ለመሆኑ ገና ምን ያህል ነው የምንጓዘው?
Andreas: አውቃለሁ፤ ጉዞው ረጅም ጊዜ ይወስዳል። ግን ግማሹን መንገድ ለመጨረስ ብዙም አልቀረንም
Ex: ምን ያህል ነው ገና መሄድ የሚኖርብን?
Andreas: አራት ሰዓታት ይቀሩናል። ነይ፤ እስቲ ወደ ምግብ ቤቱ ተሳቢ እንሂድ!

*ኢክስ ተሰላችታለች። በባቡሩ መስኮት ወደ ውጭ ስታስተውል የምታየው አንድ ዓይነት ነገር ብቻ ነው። ደኖች፤ ወንዞች፤ ሜዳ ...*

Ex: እዚህ ያሉት ደኖች፤ አበቦችና ወንዞች ብቻ ናቸው። ከተሞች የሉም፤ እንዲያው መንደሮች ብቻ! ይሰለቻል
Andreas: እንግዲያው ጥቂት ተኚ

*ኢክስ ትተኛና በርሊን ሊደርሱ ጥቂት ሲቀራቸው ትነቃለች።*

Zugführer: ፖትስዳም፤ ፖትስዳም!
Ex: ደረስን እንዴ?
Andreas: አይ፤ ግን የሚቀጥለው ጣቢያ በርሊን ነው
Ex: እሮይ!

## ምዕራፍ 17

### በርሊን ውስጥ ገና ሻንጣ አለኝ

*ይህ ምዕራፍ ሰዋስዋዊ ትንተናንም ሆነ መልመጃ ክፍልን የሚጠቀልል ባለመሆኑ ቀድም ካሉት ሁሉ ይለያል። በድምጽ ስብስቦች ወይም ጥንቅሮች አማካይነት የሚቀርበው ስርጭት የበርሊንን ጥንታዊና ወቅታዊ ገጽታ ያንጸባርቃል።*
*የድምጹ ስብስብ የሚከተሉትን ይጠቀልላል፤*

1. በ 1930 በርሊን ውስጥ የተቀረጸ የፔተር ኢገልሆፍ ሙዚቃ „*Das Spatzenkonzert*“ አንድ ክፍል

2. ዝነኛው ዜማ „*Das ist die Berliner Luft*“ ሙዚቃውን በ 1930ዎቹ የተጫወተችው ሊትሲ ቫልድሞለር ነበረች

3. የ Comedian Harmonists ሙዚቃ! በጊዜው በየቲያትር ቤቱ ይቀርብ የነበረው ቡድን እጅግ ዝነኛና ተወዳጅ ነበር። „*Mein kleiner grüner Kaktus*“ የተሰኘችውን የመሳሰሉት ብዙዎች ዜማዎቹ ዛሬም የተወደዱ ናቸው። ቡድኑ ሶስት ባልደረቦቹ አይሁዳውያን ስለነበሩ በይፋ ትርዒቱን እንዳያሳይ በ 1934 በናዚዎች ይታገዳል

4. የራዲዮ መልዕክት በዝነኛው የጀርመን ደራሲ ቶማስ ማን (1875 -1955), ቶማስ ማን በ 1933 ወደ ስዊትዘርላንድ ይሰደዳል። በ 1939 ደግሞ ወደ አሜሪካ በመሻገር 1944 ላይ የአገሪቱን ዜግነት ይወስዳል። የደራሲው መልዕክት በራዲዮ የተሰራጨው ግንበት 10- 1945፤ ማለት ናዚ ጀርመን ከተንበረከከች ከሁለት ቀናት በሁዋላ ነበር። በሕጋዊ ገደብ የተነሳ የንግግሩ ይዘት ሊሰራጭ የሚችለው በጀርመንኛ ቋንቋ ብቻ ነው

5. ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ካበቃ ከአራት ዓመታት በሁዋላ በ 1949 ዓ.ም. ጀርመን ተከፋፍላ ሁለት መንግሥታት ይፈጠራሉ። ፌደራል ሬፑብሊክ ጀርመን (ምዕራብ ጀርመን) እና ጀርመን ዲሞክራቲክ ሬፑብሊክ (ምሥራቅ ጀርመን) - በርሊንም እንዲሁ ለሁለት ትከፈላለች። በ 1961 የበርሊን ግንብ ይታነጻል። ጥቅምት 24 ቀን. 1950 ላይ አሜሪካዊው ጀነራል ክሊይ ለበርሊናውያን የነጻነት ደወል ያበረክታሉ። ይሄውም በሽነበርግ መዘጋጃ ቤት ተሰቅሎ በየለቱ ቀትር ላይ እንዲደውል ይደረግ ነበር። መጋቢት 26 ቀን. 1963 ዓ.ም. የአሜሪካው ፕሬዚደንት ጆን ኤፍ. ኬነዲይ ከተማይቱን ይጎበኛሉ። ከመዘጋጃ ቤቱ ሰገነት ላይ በመሆን (በርሊናዊ ነኝ) ሲሉ በጊዜው ለነዋሪው የተናገሯት የምትከተለው አረፍተ-ነገርም ታሪካዊ ሆና ትኖራለች።
John F. Kennedy: Ich bin ein Berliner.

6. በርሊናውያን ቀልድ በተመላበት የስላ አነጋገር ወግ የታወቁ ናቸው። የሚከተለው በአካባቢው የአነጋገር ዘዬ የቀረበ ውይይት በርሊናውያን ቀልደኞች እንደሆኑ ያመለክታል።

| | |
|---|---|
| Berlinerin: | ለግብይት መሄድ ትችላለህ? |
| Berliner: | ምን አድርግ ነው የምትይኝ? |
| Berlinerin: | ሂድ ገበያ |
| Berliner: | እኔ? ለምን እኔ? |
| Berlinerin: | ለምን አይሆንም? |
| Berliner: | ፍላጎት የለኝም |
| Berlinerin: | እኔም እንዲሁ |
| Berliner: | ተይ እንግዲህ፤ የሚበቃ ይመስለኛል- ምን? |

7. በርሊን የተለያዩ ባሕሎች መገናኛና ብዙዎች የውጭ ተወላጆች የሚኖሩባት ከተማ ነበረች፤ ዛሬም ናት። ግንቡ እስከተገረሰሰበት ወቅት ድረስ በከተማይቱ በተለይ በርከት ያሉ ቱርካውያን ነበር የሚኖሩት። የሚከተለው በስርጭታችን ውስጥ በቱርክ የአነጋገር ዘዬ የምታደምጡት ውይይት ትርጉም ነው።

| | |
|---|---|
| Türkin: | ጤናይስጥልኝ |
| Türke: | ጤናይስጥልኝ፤ ምን ይፈልጋሉ? |
| Türkin: | አንድ ዱነር „Döner“ |
| Türke : | ይሄው |

* Döner: *ከባብ – የተጠበሰ የበግ ስጋ በዳቦ (ሳንድዊች)*

8. ጀርመናዊቱ ዘፋኝና ተዋናይ ማርሊነ ዲትሪሽ! በ 1930 ዓ.ም. *„Der blaue Engel" (ሰማያዊ መልዓክ)* በተሰኘ ፊልም ታዋቂ ትሆናለች። በ 1936 ጀርመንን ለቃ ወደ አሜሪካ በመሻገር በዚያው መኖር ትጀምራለች። አሜሪካ በ 1941 ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ውስጥ እንደገባችም የአገሪቱን ሠራዊት መለያ በመልበስ በአውሮፓ ሰፍረው የነበሩትን የአሜሪካ ወታደሮች በዘፈኖቿ ታዝናናለች። እስከሞተችበት ወቅት (1992) የኖረችው በፓሪስ ነው። ሁለቱ የጀርመን መንግሥታትና በርሊን መልሰው ከተዋሃዱ በሁዋላም በትውልድ ስፍራዋ በበርሊን የመቀበር ፍላጎት እንዳላት ትገልጻለች። „በርሊን ውስጥ ገና ሻንጣ አለኝ" የሚለው ዜማዋ የተደረሰው በ 1948 ዓ.ም. ነበር። በሕጋዊ ገደብ የተነሳ ወደሌላ ቋንቋ አይተረጎምም።

**ምዕራፍ 18**

**ትሱ ባቡር ጣቢያ**

*አንድሬያስና ኢክስ ከበርሊኑ ባቡር ጣቢያ ትሱ ይደርሳሉ።*

*ማስታወቂያ በድምጽ ማጉያ*: Berlin - Bahnhof Zoo.

Andreas: ነይ ኢክስ! እዚህ መውረድ አለብን

Ex: ለምን? ወደ እንስሳት መታያ ስፍራ መሄድ ትፈልጋለህ?

Andreas: አይደለም፤ ትሱ እኮ የጣቢያው ስም ነው

Ex: ለምንድነው እንዲህ የሚጠራው?

Andreas: የእንስሳቱ መታያ እዚህ ቅርብ ስለሆነ ነው

Ex: የእንስሳት መታያ፤ ከተማ መካከል?

Andreas: አዎን፤ ምክንያቱም 150 ዓመት ሆኖታል። ያኔ ደግሞ በርሊን እንደዛሬው ትልቅ አልነበረችም

Ex: ለምን?

Andreas: ለምን? ሙዝ ለምንድነው ጠማማ የሆነው?

Ex: አላውቅም

Andreas: ብዙ ስለምትጠይቂ! በይ አሁን ነይ!

*ኢክስ የንጉሠ-ነገሥት ቪልሄልምን መታሰቢያ ቤተ-ክርስቲያን ታያለች። ቤተ-ክርስቲያኑ የሁለተኛው ዓለም ጦርነት ማሰቢያ ነው። አንድሬያስ በበኩሉ ወደ ጓደኞቹ ሄዶ ሊጠይቃቸው ይፈልጋል።*

Ex: ተመልከት! ቤተ-ክርስቲያኑ ተሰብሯል!

Andreas: አዎን፤ ፍርስራሽ ነው

Ex: ለምን?

Andreas: በጦርነቱ ጊዜ ነው የወደመው። እና እንዳለ የተተወው ጦርነቱን እንዲያስታውስ ነው። የበርሊን ነዋሪዎች ፍላጎት ነበር

Ex: ውስጥ እንግባ?

Andreas: አይ ኢክስ፤ አይሆንም። አሁን ወደ ካንት አደባባይ ነው የምንሄደው

Ex: ለምን?

Andreas: ምክንያቱም ዛሬ ማታ የምናድረው እዚያ ነው። ጓደኞቼ እዚያ ነው የሚኖሩት

Ex: እና ዶር-ትሁርማንስ?

Andreas: በሁዋላ እደውልለታለሁ

## ምዕራፍ 19

**በርሊን መሆንዎ ግሩም ነው**

*አንድሬያስ ለዶር-ትሁርማን ይደውልና ሊገናኙ ቀጠሮ ይይዛሉ። በአውቶቡስ ቁጥር አንድ መቶ በርሊንን እየተዘዋወሩ ለማየትም ይወስናሉ። አውቶቡሱ ከትሱ ባቡር ጣቢያ ተነስቶ ቀድሞይቱ ምሥራቅ በርሊን ውስጥ ወደሚገኘው ዝነኛ አደባባይ አሌክሣንደር-ፕላትስ ነው የሚሄደው።*

Andreas: እንደት አመሹ፤ ዶር-ትሁርማን! አንድሬያስ ሺፈር ነኝ
Dr. Thürmann: እንደት አመሹ፤ አቶ ሺፈር። በርሊን ነዎት እንዴ?
Andreas: አዎን፤ በርሊን ውስጥ አንድ ሣምንት ልንቆይ እንችላለን
Dr.Thürmann: በርሊን በመሆንዎ ደስ ይለኛል
Andreas: ከኔ ጓደኞች ጋር ነው የምንቆየው
Dr. Thürmann: „እኛ" ነው ያሉት?
Andreas: ኦህ፤ አያውቋም ለካ ኤክስ መመለሷን
Dr. Thürmann: በመስማቴ ደስ ይለኛል! ነገ ምን ታደርጋላችሁ?
Andreas: በርሊንን እየተዘዋወርን ለማየት እናስባለን
Dr.Thürmann: አንድ ሃሳብ ላቅርብ። በአውቶቡስ ቁጥር 100 አብረን ልንዞር እንችላለን። ከትሱ ተነስቶ ወደ ኤሌክስ ነው የሚሄደው። በርሊን ውስጥ ከሚደረገው የጉብኝት ጉዞ ሁሉ ደስ የሚለው ነው
Ex: አሌክስ? ማነው እሱ አሌክስ?
Andreas: አደባባይ ነው፤ አሌክሣንደር-አደባባይ! ይቅርታ ዶር-ትሁርማን
Dr. Thürmann: ምንም  አይደል። አንበል ነገ በአሥር ሰዓት ትሱ ባቡር ጣቢያ?
Andreas: እና በትክክል የት?
Dr. Thürmann: አውቶቡስ ማቆሚያውጋ፤ ይስማማሉ?
Ex: መልካም
Andreas: ደህና፤ እንግዲህ እስከነገ!

*ኤክስ መልዓክ መስሎ የታያትን አንድ ነገር በማግኘቷ ትደሰታለች። ለነገሩ በከተማው መለያ ቅስት ላይ ያየችው በድል አምላክነት የተመሰለ ሃውልት ነው። የበርሊኑ የድል ቅስት የፍራንኮ-ፕራሺያን ጦርነትና የጀርመንን ግዛት መመስረት እንዲያስታውስ መታሰቢያ ሆኖ የታነጸው በ 1871 ዓ.ም. ነበር።*

Ex : ተመልከት! እዚያ ላይ መልዓክ አለ
Dr. Thürmann: ኤክስ፤ የድል ቅስት ነው
Ex : ለምንድነው እንዲህ ተብሎ የሚጠራው?
Andreas: ኤክስ፤ የሚያሳዝን ሆኖ ጦርነቶች እንደሚካሄዱ ታውቂያለሽ
Dr. Thürmann: እና ባለፉት ጊዜያትም ጦርነቶች ነበሩ። ቅስቱ እንግዲህ የፍራንኮ-ፕራሺያው ጦርነት ድል መታሰቢያ መሆኑ ነው
Andreas: ይህ ከረጅም ጊዜ በፊት ነበር፤ በ 1871.
Ex: እና ከዚያስ?
Dr. Thürmann: ጀርመን ያኔ ነበር የተፈጠረችው
Ex: እንደት? ጀርመን ከዚያ በፊት አልነበረችም?
Andreas: አዎን፤ ግን በተለየ መልክ! የተመሰረተችው ብዙዎች ግዛቶችን በመጠቅለል ነው። አንድ መንግሥት አልነበረችም
Dr. Thürmann: እና ከ 1871 ወዲህ በርሊን የጀርመን ዋና ከተማ ነበረች
Ex: ነበረች ወይስ ናት?
Andreas: ሁለቱም
Ex: አይገባኝም ...

**ምዕራፍ 20**

**ግንቡ ከመምጣቱ በፊት**

*አንድሬያስ ጀርመን ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በሁዋላ ለሁለት ተከፍላ እንደነበር ለኢክስ ያስረዳል። በርሊንም እንዲሁ በምሥራቅና ምዕራብ ለሁለት ተከፍላ ነበር። ከውህደቱ በሁዋላ በርሊን እንደገና የጀርመን ዋና ከተማ ሆና ትሰየማለች። የጀርመን መንግሥትም እስከ 2000 ዓ.ም. ጨርሶ ወደ በርሊን እንዲሻገር ይወጠናል።*

Ex: በርሊን ዋና ከተማ ናት ወይስ አይደለችም?
Andreas: ደህና፣ በርሊን እስከ 1945 ዋና ከተማ ነበረች። ከዚያ በሁዋላ ሁለት የጀርመን መንግሥታት – ፌደራል ሬፑብሊክ ጀርመን (ምዕራብ ጀርመን) እና ጀርመን ዴሞክራቲክ ሬፑብሊክ (ምሥራቅ ጀርመን) ይመሰረታሉ። ሁለቱ ህያው እስከሆኑበት ጊዜ ድረስ ቦን የምዕራብ ጀርመን፣ ምሥራቅ በርሊንም የምሥራቅ ጀርመን ዋና ከተሞች ነበሩ።
Ex: እና ዛሬስ?
Andreas: ከ 1990 ውህደት ወዲህ በርሊን እንደገና የጀርመን ዋና ከተማ ናት
Dr. Thürmann: ይቅርታ፣ አቶ ሺፌር! ከመቀጠላችን በፊት የብራንደንቡርግን ቅስት ባሳይዎት ደስ ይለኛል። ይምጡ፣ አዚህ መውረድ ይኖርብናል። ዶር-ትሁርማን ለአንድሬያስ በርሊንን ከ 1961-1989 ለሁለት ከፍሎ ስለቆየው ግንብ ያወራል።

Dr. Thürmann: ይህ የብራንደንቡርግ ቅስት ነው። ግንቡ እዚህ ነበር። እኔ ወደ በርሊን ስመጣ ግንቡ አልነበረም። እና ከዚያ ድንገት በአንድ ሌሊት ገሃድ ይሆናል። አስከፊ ነገር ነበር። ይህ ስፍራ ግንቡ ከመታነጹ በፊት እንቅስቃሴ የበዛበት የደመቀ ቦታ ነበር። በቅስቱ ውስጥ በማለፍ ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ-ከምዕራብ ወደ ምሥራቅ መሄድ አዳጋች አልነበረም። ግን ከዚያ በሁዋላ ድንገት የማይቻል ነገር ይሆናል። ግንቡ በዚህ ስፍራ ሰላሣ ዓመታት ገደማ ነው የቆየው። አቋርጦ መሄድ የሚቻል ነገር አልነበረም። በቀላሉ መንገዶቹ የተዘጉ ነበሩ።
Ex: ግንቡን ጨርሶ አላይም
Dr. Thürmann: የማይታይ ነው፣ ልክ እንዳንቺው ኢክስ። ማስታወሻ ብቻ ነው ...
Berliner Ausrufer: አንዲት ቁራጭ ግንብ፣ በተለይ ለርስዎ፣ አንዲት ማስታወሻ!
አንዲት ቁራጭ ግንብ፣ ሶስት ማርክ ብቻ! አሁን ይግዙ!
አንዲት የግንብ ቁራጭ፣ አይዘግዩ - ከማለቁ በፊት!

**ምዕራፍ 21**

**ሁሉም ነገር በጣም እየተወደደ ነው የሚሄደው**

*አንድሬያስ ከአንዳንድ በርሊናውያን ጋር ቃለ-ምልልስ አድርጓል። የጠየቀው ሰዎቹ የጀርመን ፌደራል ምክርቤት በርሊንን መልሶ የጀርመን ዋና ከተማ ለማድረግ ያስተላለፈውን ውሳኔ እንዴት እንደሚመለከቱ ነበር። አንዲት በርሊናዊት በዕርምጃው በጣም ተደስታለች።*

Andreas : በርሊን እንደገና የጀርመን ዋና ከተማ ልትሆን ነው። ምን ያስባሉ?
Berlinerin: እኔ ምን እንደማስብ? ግሩም ነው! እንደገና ታላቅ ከተማ ...

*አንድሬያስ ከዚያም አንድ በርሊናዊን ይጠይቃል። ሰውዬው በርሊን ዋና ከተማ መሆኗ ጉዳት ያስከትላል ባይ ነው።*

Berliner: ጥሩ መስሎ አይታየኝም። መኖሪያ ቤቶች የበለጠ ይወደዳሉ፣ ምግብ፣ መጓጓዣ፣ ሁሉም ነገር በጣም ነው ውድ የሚሆነው። ጉዳት ብቻ ያለው ይመስለኛል

*አንድሬያስ ቀጥሎም አንድ ታክሲ ነጂን ያነጋግራል። ሰውዬው ዋና ከተማ መሆኑ ለበርሊን ጥቅም አለው ብሎ ነው የሚያምነው።*

Taxifahrer: እንደ ታክሲ ነጂ አንዳች ተቃውሞ የለኝም። ጥቂት ተጨማሪ ገቢ ላገኝ እችላለሁ። እና በርሊንም ዓለምአቀፍ ከተማ ትሆናለች። ባዕድ ቋንቋ መማር የሚኖርብኝ ይመስለኛል

*አንድሬያስ አንድ ጠና ያሉ ሴትን ያነጋግራል። እርሳቸው ውሳኔው ለአውሮፓ ባለው ጠቀሜታ ላይ ነው ያተኮሩት።*

Ältere Dame: ጥሩ ውሳኔ ነው ብዬ አስባለሁ። በዕውነት በጣም ግሩም! እና ለምን እንደሆነ ታውቃለህ? ምክንያቱም ለአውሮፓ ጥሩ ነው። በርሊን ምዕራብ አውሮፓ ውስጥ ብትሆንም ለምሥራቁም ክፍል የቀረበች ናት። ስለዚህም ከምሥራቅ የምታገናኝ ድልድይ ልትሆን ትችላለች

*አንድ ወጣት በበኩሉ በርሊን የለዘብተኝነት ገጽታዋን እንዳታጣ ይሰጋል።*

Jugendlicher: ጨርሶ ጥሩ ነው ብዬ አላስብም። የነበረው የለዘብተኝነት ባህርይ ብዙ ሳይቆይ ነው የሚጠፋው። ወደ በርሊን የመጣነው እዚህ ብዙ ነጻነት በመኖሩ ነበር። ያስገርም ይሆናል፣ ግን በርሊን ውስጥ በእርግጥ ብዙ ነጻነት ነው የነበረው።

**ምዕራፍ 22**

**በርሊን አሌክሣንደር አደጣይ**

*አንድሬያስ ለወላጆቹ ደብዳቤ ይጽፋል። ለወላጆቹ የሚገልጸው ምሥራቃዊው በርሊን ውስጥ የሚገኘውን Alexanderplatz -ን ሲጎበኝ ያደረበትን ስሜት ነው።*

የደብዳቤው ይዘት የሚከተለው ነው:
ወድ ወላጆቼ፣

ትናንት ምሥራቅ በርሊን ነበርኩ፣ ዘነኛው አሊክሣንደር-አደባባይ ላይ። ከፍተኛው የቴሌቪዥን ማቀባበያ ሕንጻ ገና ከሩቅ ነው ጎልቶ የሚታየው። 365 ሜትር ከፍ ያለ ነው! ግን ሃቁን ልናገርና ያን ያህል እርካታ አልተሰማኝም። አሌክስ ትልቅ፣ ግዙፍ አደባባይ ነው። ግን ታዲያ ባዶ ነው። መኪናዎች የሉም፣ ጥቂት እግረኞች ብቻ ናቸው ሲንቀሳቀሱ የሚታዩት። እርግጥ አሊክስ ከ 1964 ወዲህ ብዙ መለወጡን አውቃለሁ። ያኔ ብዙ ሕንጻዎች ይሰሩ ነበር፣ ለምሳሌ አስቀያሚው ሆቴል *Stadt Berlin* ! ሊሎቹም ሕንጻዎች ያስደንቁ እንጂ እንዲሁ ...
በአሌክሣንደር አደባባይ ባቡር ጣቢያ አጠገብ ያለው ሁኔታ ግን ጨርሶ ለየት ያለ ነው። አዎን፣ አሮጌው ጣቢያ ዛሬም አለ። እና አካባቢው ሕይወት የተመላበት ነው። ከጣቢያው ውጭ ብዙ መደብሮች አሉ፣ መዓት ነገር መግዛት ይቻላል። አልባሳት፣ የቤት ዕቃ፣ ፍራፍሬ፣ አትክልት፣ ምግብ ...

አደባባዩ ለምን አሌክሣንደር-ፕላትስ እንደተባለ ታውቃላችሁ? አታውቁም? ደህና፤ ግን እኔ! የሩሢያው ሣር አሌክሣንደር ቀዳማዊ በ 1805 ወደ በርሊን መጥቶ የፕራሺያውን ንጉሥ ሲጎበኝ ነበር አደባባዩ በስሙ እንዲጠራ የተደረገው።

*አንድሬያስ ቀድሞ አሌክሣንደር-አደባባይ ላይ ሕይወት እንዴት እንደነበረ ለማሰብ ይሞክራል።*

*በደብዳቤው በመቀጠልም:*

በቀድሞው ጊዜ አሌክስ በዕውነት የበርሊን ማዕከል ነበር። ዘጠኝ መንገዶች በዚያው ነበር የሚገናኙት፤ እና ሁሉም ቦታ ሰው በብዛት ያታይ ነበር። አደባባይ ላይ ሆነው ዕቃዎቻቸውን-ጋዜጦች፣ ትምባሆ፣ አልባሳት፣ ከሰል፣ አንጨት ... ይሸጡ ነበር። በየቡና ቤቱ ሆነው ቢራ ይጠጡ፤ ያወሩ፤ በጣምም ይሰሩ ነበር።
ይህን ሁሉ ከየት ነው ያወቅሁት? አልፍሬድ ዶብሊን የደረሰውን *„Berlin Alexanderplatz“* የተሰኘ መጽሃፍ ገዝቻለሁ። አሌክስ ላይ ይገኝ ስለነበረ አንድ ተራ የመንገድ ሽቃጭ ነው የሚያወሳው። በቁራጭ ዳቦ ከተወሰነች ኑሮው የተሻለ ሕይወት እንዲኖረው ይፈልግ ነበር።... ይህን መረዳት አያዳግትም፤ አይደል? ዛሬ ማምሻውን *„Berlin Alexanderplatz“* የተሰኘውን የፋስቢንደርን ፊልም ለማየት እሄዳለሁ። እንደምታዩት እዚህ ጥሩ ተስማምቶኛል።

ከፍቅር ሰላምታ ጋር፤
አንድሬያስ

**ምዕራፍ 23**

**ዝነኛው ሻሪቴ**

*አንድሬያስ፣ ኤክስና ዶር-ትሁርማን ምሥራቅ በርሊን ውስጥ ናቸው። ዶር-ትሁርማን አንዴ ይሰራበት ከነበረው ዝነኛ ሆስፒታል ከሻሪቴ ፊትለፊት ቆመዋል። የሆስፒታሉ መጠሪያ ስም ከየት እንደመነጨ ይወያያሉ።*

| | |
|---|---|
| Ex: | ተመልከት እዚያ ላይ – በትልቁ የተጻፉትን ፊደሎች! *(ፏክ ብላ ታነባለች)* ሻ - ሪ - ቴ,. |
| Andreas: | ሻሪቴ፣ ኤክስ-ሻሪቴ! |
| Dr. Thürmann: | አዎን፤ ዝነኛው ሻሪቴ ነው። በዓለም የታወቀ ሆስፒታል! አንዴ እዚያ እሰራ ነበር |
| Andreas: | እና ለምንድነው ሻሪቴ የሚባለው? |
| Dr. Thürmann: | በትክክል አላውቅም። መገመት ብቻ ነው የምችለው። ሻሪቴ በጣም የቆየ ነው። 300 ዓመት ገደማ ይሆነዋል። እና በ 1710 በተመሰረተበት ጊዜ ብዙ ፈረንሣዮች በርሊን ውስጥ ይኖሩ ነበር። |
| Ex: | አሃ፤ ሻሪቴ እንግዲህ የፈረንሣይ ቃል መሆኑ ነው? |
| Andreas: | አዎን |
| Ex: | እና ምን ማለት ነው? |
| Andreas: | በጎ አድራጎት |
| Ex: | ምን አልክ? |
| Andreas: | ለድሆች ማዘንና መርዳት |

*ዶር-ትሁርማን የሻሪቴን ታሪክ ያስረዳል።*

Andreas: ለምንድነው ሻሪቴ እንዲህ ዝነኛ የሆነው?

Dr. Thürmann: ሻሪቴ በዓለም ላይ የታወቀ የምርምር ማዕከል ነበር። ገና ቀድሞ ነበር ከባድ የቀዶ ጥገና ሕክምና የሚሰጠው። እርግጥ ይህ ብቻ አይደለም። ነጻ ምርምርም ይካሄድ ነበር። በሆስፒታሉ ግሩም ሃኪሞች ይሰሩ ነበር፤ እና በርካታ የኖቤል ሽልማቶችን አግኝተዋል

Andreas: ግን አሁን ሁሉም ነገር ያረጀ ይመስላል

Dr. Thürmann: እርግጥ ነው! በናዚዎች ዘመን አይሁዳውያን ሃኪሞች መሄድ ነበረባቸው። ቆየት ብሎም ጥሩ የህክምና ዘዴም ነበር። ግን እንደቀድሞው ብዙ ምርምር ማካሄዱ ቀርቷል

Andreas: እና ዛሬስ?

Dr. Thürmann: ወጣት ሃኪሞች አዲስ ጥረት እያደረጉ እንደሆነ ስምቻለሁ። ይህን የቀድሞ ታሪክ ያለውን ቤት እንደገና ለማንቃቃት ይፈልጋሉ።

Andreas: አዲስ መንፈስ በአሮጌ ግንቦች ውስጥ?

Dr. Thürmann: አዎን፤ እንደዚያ ሊባል ይችላል

## ምዕራፍ 24

### *ሙታን ሁልጊዜ ሙታን አይደሉም*

*አንድሬያስ ምሥራቅ በርሊን ውስጥ የሚገኘውን ዝነኛ መካነ-መቃብር* Dorotheenfriedhof *-ን ለማየት ይፈልጋል። በርከት ያሉ ታዋቂ ጀርመናውያን፤ ለምሳሌ ፈላስፎቹ ፊሽተና ሄገል፤ ደራሲያኑ ቤርቶልት ብሬሽትና ሃይንሪሽ ማን፤ ሙዚቀኛው ሃንስ አይዝለርና ተዋናይቱ ሄሌን ቫይገል በዚያ ነው የተቀበሩት። ... ኢክስና አንድሬያስ ይህንኑ መካነ-መቃብር እየተዘዋወሩ ይታዘባሉ። እርግጥ ኢክስ አንድሬያስን ወደዚህ ስፍራ የሳበው ምክንያት ምን እንደሆነ ለማወቅ ትፈልጋለች።*

Andreas: ዛሬ ወደ ዶሮቴ መካነ-መቃብር ለመሄድ እፈልጋለሁ

Ex: መካነ-መቃብር?

Andreas: ሙታን የሚቀበሩበት ቦታ ነው። ይህን አታውቂም?

Ex: እና እዚያ ከሙታን ጋር ምን ማድረግ ትፈልጋለህ? ከሙታን እኮ መነጋገር አትችልም!

Andreas: ኦህ፤ ኢክስ! እንዴት አድርጊ ላስረዳሽ? ሙታን ሁልጊዜ ሙታን አይደሉም። አንዳንዶቹ በአይምሮዬ ውስጥ ይኖራሉ። በዘፈናቸው፤ በድርሰታቸውም እንዲሁ! ትመልሺ?

Ex: አዎን፤ ላየው እፈልጋለሁ። ከዚህ ቀደም ወደ አንድ መካነ-መቃብር ሄጄ አላውቅም። ኢክስ በመቃብር ድንጋዮች ላይ የሰፈሩትን ስሞች ታነባለች። በምዕራፍ 24 የራዲዮ ስርጭት በዚህ ስፍራ የዘላለም ዕረፍታቸውን ካገኙት ዝነኛ ሰዎች ስራ የተውጣጣ ይዘትን ታደምጣላችሁ።

Ex: *(ጮክ ብላ ታነባለች)* ዮሃን ጎትሊብ ፊሽተ ከ 1762-1814፤
ጌኦርግ ቪልሄልም ሄገል ከ 1770-1831፤
ቤርቶልት ብሬሽት ከ 1898 - 1956...

Andreas: *(ከብሬሽት ግጥም "An die Nachgeborenen" ይጠቅሳል)*

Ex: *(ማንበቧን በመቀጠል)* ሄሌነ ቫይገል–ብሬሽት ከ 1900 -1971

| | |
|---|---|
| | *የሙዚቃ ክፍል: ሄሌን ቫይገል ከቤርቶልት ብሬሽት ድርሰት „Mutter Courage und Ihre Kinder" የደፋሯን እናት ዜማ ታዜማለች* |
| Ex | *(ፎኬክ ብላ ታነባለች)* ሃንስ አይዝለር ከ 1898 - 1962 የሙዚቃ ክፍል: ቴሬዘ ጊህዘ „Die Ballade vom Wasserrad" የተሰኘውን ዘፈን ታዜማለች። ሙዚቃው የተቀናጀው ለብሬሽት ድርሰት *„Die Rundköpfe und die Spitzköpfe"* ሲሆን የተደረሰው በሃንስ አይዝለር ነበር |
| Ex: | *(ፎኬክ ብላ ታነባለች)* ሃይንሪሽ ማን ከ 1871 - 1950<br>ምንባብ: *„Professor Unrat"* የተሰኘው የሃይንሪሽ ማን ልብወለድ ድርሰት በ 1930 *„Der blaue Engel"* የተሰኘ ፊልም ይሰራበታል።<br>ማርሌን ዲትሪሽ የፊልሙን ገዝኛ ዜማ *„Ich bin von Kopf bis Fuß auf Liebe eingestellt"* ትጫወታለች |

**ምዕራፍ 25**

**በመጀመሪያ አንስተኛ ስራ አገኛለሁ ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ**

*አንድሬያስና ዶር-ትሁርማን ስለወደፊት ዕቅዳቸው ይወያያሉ። ዶር-ትሁርማን በአማራጭ የህክምና ዘዴ ላይ አንድ መጽሃፍ ሊጽፍ ያስባል። አንድሬያስ በዚሁ ተግባር በምርምር ሊረዳው ፈቃደኛ እንደሆነም ይጠይቃል።*

| | |
|---|---|
| Dr. Thürmann: | መልካም፤ እንደገና ወደ በርሊን እንኳን ደህና መጡ! ይቀመጡ! |
| Ex: | እኔም? |
| Dr. Thürmann: | አዎን አንቺም፤ አንቺ የማትታዪ ነገር! በርሊንን ብዙ አይተናል፤ ግን ስለራሳችን ምንም አላወራንም። እንዴት ነዎት? ትምሕርቱስ እንዴት ነው? |
| Andreas: | አመሰግናለሁ፤ እኔ ደህና ነኝ። ትምሕርቴንም በቅርቡ እጨርሳለሁ |
| Dr.Thürmann: | ከዚያስ? ከዚያ ምን ያደርጋሉ? |
| Andreas: | ገና አላውቀውም። ለጋዜጣ ወይም ራዲዮ የመስራት ሃሳብ አለኝ። ግን በትንሽ ስራ ለመጀመር ነው የምፈልገው |
| Dr. Thürmann: | ምናልባት በኔ ስራ ሊረዱኝ ይችላሉ? |
| Andreas: | በደስታ! |
| Dr. Thürmann: | ያውቃሉ፤ ስለ አማራጭ የህክምና ዘዴ መጽሃፍ ልጽፍ እፈልጋለሁ |
| Andreas: | ምን ማለትዎ ነው? |
| Dr.Thürmann: | ሆሜኦፓቲ ማለቴ ነው። በተፈጥሮ ዘዴ መፈወስን በጣም አምንበታለሁ። እና ቃለ-መጠይቆች ያስፈልጉኛል። ታዲያ ለኔ መረጃ ለመሰብሰብ ፈቃደኛ ነዎት - ከሃኪሞችና ከህመምተኞች ጋር ቃለ-ምልልስ ማድረግ፤ ጸሁፎችን መፈለግ? |
| Andreas: | በደስታ ማድረግ እፈልጋለሁ። ግን እንደገና በትክክል ሊያስረዱኝ ይገባል |

*ዶር-ትሁርማን ስለሚያክማቸው ሰዎች ያወሳል። ምናልባት ኢክስ እንድትትይ ማድረግ እንደሚችልም በቀጥታ አይሁን እንጂ ለአንድሬያስ ፍንጭ ይሰጣል*

| | |
|---|---|
| Andreas: | አንዴ ሻሪቴ ሆስፒታል ውስጥ ይሰሩ እንደነበር ነግረውኛል |
| Dr. Thürmann: | አዎን፤ ግን ከረጅም ጊዜ በፊት ነው። ያኔ ገና ወጣት ነበርኩ |
| Andreas: | ምን ነበር የሚሰሩት? |
| Dr.Thürmann: | ብዙ፤ ብዙ ነገር! የራሴ የግል ክሊኒክ ነበረኝ፤ አስከዛሬም አለኝ። ገና ታካሚዎቼ ብዙዎች ናቸው፤ ወጣትና ሽማግሌ! ግሩም ነገር ነው |

| | |
|---|---|
| Ex: | ህመምተኞች ግሩም ናቸው? |
| Dr. Thürmann: | የለም፣ ኢክስ! እንደሱ ማለቴ አይደለም። ስራው ጥሩ ነው። ሰዎችን መርዳት እችላለሁ፣ ምናልባት አንቺንም ልረዳሽ እችላለሁ! |
| Ex: | እኔን? ለምን እኔን? |
| Dr. Thürmann: | ምናልባት የምትታዩ ላደርግሽ እችል ይሆናል? |
| Ex: | የለም፣ የለም፣ የማልታይ ሆኜ መቅረት ነው የምፈልገው |
| Andreas: | ግን እኔ ላይሽ እፈልጋለሁ! |
| Ex: | እኔ ግን አልፈልግም! |

**ምዕራፍ 26**

***በቀላሉ አብረን መሆን ብቻ ነው የምንፈልገው***

*በዚህ ምዕራፍ የጀርመኑን ዘፋኝ የኡዶ ሊንደንበርግን ዜማ ታደምጣላችሁ። የዜማው ይዘት አይተረጎምም።*